# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 44 መጋቢት 10 2001 ዓ.ም

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

መለስ ዜናዊ አስራ ስምንት ዐመት ሙሉ ቢፍቀዉ ቢፍቀዉ አልጠፋልህ ያለዉን የኢትዮጵያዊነት መንፈስ ዛሬ እስላምና ክርስቲያን በሚል እሳት ሊያቃጥለዉ እየሞከረ ነዉ።

## ከዝግጅት ክፍላችን

ገጽ 3 ላይ ይመልከቱ

## ያራ ውለታው እየተከፈለው መሆኑ ታወቀ

ከሰኔ አንድ 1997 ጭፍጨፋ በኋላ ሀምሌ1997 አ.ም ለዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ የአረንጓዴው አብዮት አራማጅ በሚል ሽልማት ሰጥቶ የነበረው ያራ የተባለ የማዳበሪያ አምራች ኩባንያ ሰባ አምስት ሺህ ሜትሪክ ቶን ማደባሪያ እንዲያስገባ ባሳለፍነው ሳምንት የተፈቀደለት መሆኑ ተዘገበ። የወያኔ አባል መሆናቸውን በአደባባይ በኩራት የሚናገሩት ሼክ መሀመድ አላሙዲን የተወሰነ የባለቤትነት ድርሻ (ሼር) እንዳላቸው የሚነገርለት ይህ የማዳበሪያ ኩባንያ መለስ ዜናዊን ኖርዌይ ድረስ ጠርቶ ሽልማት መስጠቱ እንደውለታ ተቆጥሮለት ሳይሆን አይቀርም ጨረታውን እንዲያሸንፍ የተደረገው ተብሏል። በመለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትዕዛዝ በጠራራ ጸሃይ የተጨፈጨፉት ንጹሃን ዜጎቻችን ደም ገና ባልደረቀበት በዚያን ሰዓት ያራ ባዘጋጀው ሽልማት ላይ አንድም የኖርዌይ ባለስልጣን ያልተገኘ እንደነበር እና መለስ ዜናዊን መሰል ነፍሰ ገዳይ በአገራቸው ምድር ለሽልማት መብቃቱ እንደሚያሳፍራቸው እንዳንድ የአገሪቱ ከፈተኛ ባለስልጣናት እንደገለጹ በወቅቱ የተለያዩ የዜና አውታሮች መዘገባቸው ይታወሳል።

በአሁን ጊዜ በአገሪቱ ውስጥ የሚካሄዱ ማንኛውም ጨረታዎች ለወያኔ ባለሥልጣናት ከፍተኛ የመደለያ ገቢ በውጭ ሚንዛሪ ሊሰጡ በሚችሉ የውጪ ሀገር ድርጅቶች ብቻ እንደሚጨረቱ የሚታወቅ ሲሆን ለበርካታ አመታት ለኢትዮድያ ገበሬዎች ማዳበሪያ በማቅረብ ይታወቅ የነበረው ሀገር በቀሉ የማደበሪያ ኩባንያ አማልጋሜትድ በወያኔ በተሰራበት ደባ ሆነ ተብሎ ከገበያ እንዲወጣ መደረጉ ይታወሳል። እንደ አማልጋሜትድ ያሉ አንጋፋ ድርጅቶች በተሰራባቸው ደባ መዘጋታቸው ለውጪ ድርጅቶች እና ከወያኔ ጋር ለሚሞዳሞዱ የውጪ ሀገር ባለሀብቶች ትልቅ እድል መፍጠሩን ታዛቢዎች ይናገራሉ።

ይህ በእንዲህ አንዳለ ወያኔ በምንተዳዬ ስሜት ለሳውዲ አረቢያ ከበርቴዎች በብዙ ሚልዮን ዶላር የሸጠው ለም የእርሻ መሬት ላይ የተዘራው የእርሻ ምርት አብቦ እና አሽቶ ተሰብስቦ የሀገሪቱ መዲና ሪያድ መድረሱን ዘገባዎች እያመለከቱ ነው።ፋይናንሻል ታይምስ የሳውዲን መንግስት ጠቅሶ እንደዘገበው ይደርሳል ተብሎ ከተጠበቀው ጊዜ በታች በአፋጣኝ የደረሰው የሩዝ ምርት የሀገሪቱ ንጉስ አብዲላሂ ጋር ቀርቦአል። በርካታ ሚልዮን ዜጎቿ ለተደጋጋሚ የረሃብ አደጋ የተጋለጡባት ኢትዮጵያ ለም መሬቷን ለባእድ አሳልፋ በማስጠት በነዳጅ ሃብቷ ወደር የሌላትን ሃብታም አገር ለመመገብ መዘጋጀቷ እንቆቅልሽ ነው ያለው የዜና ምንጭ በኢትዮድያ የተጀመረው የሳውዲ እርሻ ተራውን ህዝብ መጥቀሙ በእጁጉን አጠራጣሪ መሆኑን የመሰኩን ባለሙያዎችን አነጋግሮ ገልጿል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## መለስ እያደግሁ ነው ይላል.....ፋብሪካዎች ሲራ እያቆሙ መሆኑ ታወቀ

የኢኮኖሚ ቀውሱ ተባብሶ የኮካ ፋብሪካ ማምረት ባቆመ ማግስት አንጋፋው የሀረር ቢራ ፋብሪካ በከፊል ምርት ማቆሙ ተዘገበ። የሀረር ቢራ ተወዳጅ ምርት የነበረው ከአልኮል ሙሉ በሙሉ ነጻ የሆነውን ሀረር ሶፊ የተባለውን መጠጥ ማምረት ፋብሪካው ሙሉ በሙሉ ሲያቆም፣ ሀረር ቢራ እና ሀረር ስታውት የተባሉት መጠጦች ምርት ደግሞ ከግማሽ በላይ መቀነሱ ታውቋል። በሀገሪቱ በደረሰው ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ እጥረት የተነሳ የሚዘጉ ፋብሪካዎች በተለይ በቅርቡ ቁጥራቸው እንደሚጨምር የተገመተ ሲሆን ሀረር ቢራም የዚሁ ሰለባ መሆኑ ተገልጿል።

የሀረር ሶፊን ጠርሙስ የሚያመርተው ኩባንያ በደረሰበት የውጪ ምንዛሪ እጥረት ተፈላጊ እቃዎችን ከውጪ ሀገር ማስገባት እንዳቃተው እና ምርት ለማቆም እንደተገደደ ተዘግቧል።
በርካታ ፋብሪካዎችን ባዳረሰው የኢኮኖሚ ቀውስ በደሌ ቢራ ፋብሪካም በውጪ ምንዛሪ እጥረት ሳቢያ ምርቱን በግማሽ ለመቀነስ መገደዱ ታውቋል።

በደሌ ለምርቱ የሚጠቀመውን ማልት እና ኬሚካልን ለመግዛት የውጭ ምንዛሪ እንዲፈቀድለት ቢያመለክትም ላለፉት 3 ወራት ማግኘት እንዳልቻለ ተገለጿል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአፍሪካ በታላቅ ገበያነቱ በሚታወቀው መርካቶ ከውጪ ሀገር የሚገቡ እቃዎች ለምልክት እንኳን እንደማይገኙ የግንቦት ሰባት ዘጋቢ በመርካቶ ተዘዋውሮ ማረጋገጡን በዘገባው ገልጿል። እንደ ዘገቢያችን ገለፃ፥ በርካታ ነጋዴዎች የውጪ ምንዛሪ ማግኘት አዳጋች ሆኖባቸዋል። “አንድ መቶ ሺህ ዶላር የሚያወጣ እቃ ለማምጣት የሚያስችለውን የውጪ ምንዛሪ ለማግኘት እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር ጉቦ መክፍል ግድ ይላል” ያሉት ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው የመርካቶ ነጋዴዎች፣ የውጪ ምንዛሪውን ለማግኘት ከጉቦ በተጨማሪ ከወያኔ ጋር በተለያየ ሁኔታ ቅርበት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

## እነመለስ እየተሸበሩ መሆኑ ተገለጸ

የአምባገነኑ መለስ ዜናዊ አገዛዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአሜሪካ መንግስት በኢትዮጵያ ላይ ያወጣዉን የሰብዓዊ መብት ሪፖርት በተመለከተ ለሁለተኛ ጊዜ መግለጫ አወጣ ፣ መግለጫው አገዛዙ ያለበትን መርበድበድ የሚገልጽ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ተያይዞት ያለውን ሃሰት የመርጨት ዘመቻ አካል እንደሆነ ታወቀ::

የወያኔ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መጋቢት 1 ቀን ለሁለተኛ ጊዜ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ መግለጫ ማውጣቱ አገዛዙ ያለበትን መደናበር እንደሚያሳይ አንዳንድ ታዛቢዎች ይናገራሉ። ከስምንት ደቂቃ በላይ የፈጀውና በፈረደበት የኢትዮጵያ ቴለቪዥን አገልግሎት ዜና አንባቢ የተነበበው መግለጫ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በውሸት የተሞላና ሪፖርቱን አግኝተው ለማንበብ የማይችሉ ዜጎችን ለማሳሳት ሆን ተብሎ የተጻፈ ይመስላል ብሎአል ዘጋቢያችን ስለ ሁኔታው ያነጋገራቸውን ሰዎች አስተያየት ጠቅሶ የላከልን ዘገባ።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ለጎረቤት ሲነገር ለኔ ብለህ ስማ!

የአለምአቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት ከስልጣን የወረዱትን የአፍሪካ ገዥዎች ብቻ ሳይሆን በስልጣን ላይ ያሉትንም በሰው ልጆች ላይ ፈጸሙት በሚለው ወንጀል ከሶ ለፍረድ ለማቅረብ ፍላጎት እንዳለው በሰሞኑ ውሳኔው ግልጽ አድርጎታል፡፡ የእዚህም ማስረጃ ባለፈው ሳምንት የሱዳኑ ፕሬዚደንት ኡመር አልበሺር ለፍርድ እንዲቀርቡ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት የቆረጠው የፍርድ ቤት መጥሪያ ነው፡፡

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት "እርምጃው በዳርፉር የተጀመረውን የሰላም ሂደት አደናቃፊ ነው" ብሎ፣ የተባበሩት መንግስታት የፀጥታ ምክርቤት በውሳኔው ላይ እገዳ እንዲያደርግ ጥሪ ሲያደርግ፣ "ነግ በኔ" ብሎ ሲባንን የሚያድረው ዘረኛው ነብሰገዳይ መለስ ዜናዊ ደግሞ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ አውግዞታል፡፡ አዎን! መለስ ለአመታት በኢትዮጵያ ያካሄደው ብካይ የተደበቀና ከአለም ህብረተሰብ የተሰወረ ነው ብሎ ቢፅናናም፣ በሞቃዲሾ ያካሄደው ፍጅትና በቀጣይነት በኦጋዴን ላይ የሚፈፅመው እልቂት ግን የምዕራቡን ሚዲያ ትኩረት የሳበና፣ ውሎ አድሮም ተጠያቂ ሊያደርገው እንደሚችል የተረዳ ይመስላል ። የወያኔ አገዛዝም ለፍርድ ቤቱ ያሰማው ተቃውሞ መነሻ የነገ ባለተራ ሊሆን እንደሚችል ፍንትው ብሎ ስለታየው መሆኑ አያጠራጥርም ።

ፍትህ ዕውር ናት የሚባለው ያለምክንያት አይደለም ። ሀብት ጉልበትንና ስልጣንን ተገን አድርገው በህዝብ ላይ፣ በደካሞች፣ በህፃናትና አረጋውያን ላይ ግፍ የሚፈፅሙ ይዋል ይደር እንጂ የፍትህ ሰይፍ የሚያርፍባቸው ለመሆኑ አያጠያይቅም። በዘመናችን ያየነውን የቀዳማዊ ሃይለስላሴን በአብዮት መገልበጥና ራሳቸው ባሳደጉዋቸው የጦር መኮንኖች መገደል ላስተዋለ፣ ቀጥሎም ደርጉ ለ17 አመታት በሃገራችን ላይ ላወረደው አበሳና ለደረሰበት ስደትና እስራት ዛሬም መንግስቱ ሃይለማርያም "ካሁን አሁን ተይዤ ታሰርኩ" ብሎ የሚባንንበትን ህይወት ለተመለከተ፣ አእምሮ ያለው ሰው ተመልሶ ግፍና ጭፍጨፋ ውስጥ ይገባል ብሎ መገመት ከባድ ነበር ።

"ድሃ ተበደለ፣ እኩልነት ጠፋ" ብሎ የተነሳው ወያኔ ግን "ለምን ተቃናቃኞቼን መረጣችሁ" ብሎ በሰኔ 97ና በጥቅምት 98 የ193 ዜጎችን ህይወት ማጥፋቱ ያስተማረን ነገር ቢኖር፣ ስልጣን ለብልግና፣ ፍፁም ስልጣን ደግሞ ለፍፁም ብልግና የሚዳርግ መሆኑን ነው ። ለዚህም ነው ስልጣን ገደብ የሚያስፈልገው ። የሚዲያና የፍርድ ቤት ነፃነትም ጥቅም አንዱ፣ ባለስልጣኑ ራሱን ወደ ማጥፋት አደጋ ውስጥ ከመውደቁ በፊት ሊያርቁት የሚችሉ ሃይሎች በመሆናቸውም ጭምር ነው ። ወያኔ ግን በተፃራሪው ይበልጥ ወደ ገደል የሚገፋውን ቁልቁለት በመምረጥ፣ ከምርጫ 97 ወዲህ ህገ-ወጥነቱን እያጠበቀ፣ እብሪቱን እያሳበጠ በመሄድ ላይ ይገኛል ።

በግንቦት ሰባት ንቅናቄ እምነት፣ በወንጀል ላይ ወንጀል መጨመር፣ መፍትሄ አይመስለንም ። ላለፈው ይቅርታ ጠይቆ፣ ለወደፊት ላለመድገምም ተፀፅቶ ማለቂያን ማሳመር የተሻለ ነው እንላለን ። የወያኔ መሪዎች አለም አቀፍ ፍርድ ቤቱን ስለኮነኑ ብቻ በሰሩት ወንጀል በእዚህ ፍርድ ቤት ከመከሰስና ቅጣታቸውን ከመቀበል ሊያመልጡ አይቻላቸውም፡፡ ይህ ማለት የኢትዮጵያ ህዝብ ከአለም አቀፍ ፍርድ ቤቱ ቀድሞ አይቀጣቸውም ማለት አይደለም፡፡ በውስጥ መሸሸጊያና ወደ ውጭ ወጥቶ መደበቂያው እያለቀባቸው የሚገኙት የወያኔ መሪዎች ከገበቡት አጣብቂኝ መውጣት የሚችሉት በሃገርና በወገን ላይ ለፈጸሙት ወንጀል በኢትዮጵያ ህዝብ ፊት ንስሃ ሲገቡና ሃገሪቱንና ስልጣናቸውን ለህዝብ ሲያስረክቡ ብቻ ነው ። በያዙት ከቀጠሉ ግን መዋረድ ላይቀርላቸው ነው ። የሰሞኑ የአለም አቀፉ ፍርድ ቤት ደወል የቃጨለው፣ ማነህ ባለሳምንት እያለ የሚደውለውም ይህ የውርደት ቀን መቃረቡን ለመለስና ለጓደኞቹ ለማርዳት ነው፡፡ የግንቦት 7 ንቅናቄ ጆሮ ያለው ይስማ ይላል!

## ያራ ውለታው ...

( ከገጽ 1 የዞረ)

የኢትዮጵያ ገበሬ የሚያርሰው መሬት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያነሰ እየሄደ ባለበት በዚህ ጊዜ ወያኔ መሬታችንን ለውጪ መንግስታት በገፍ መስጠቱ አስጨናቂ ነው ያሉት ታዛቢዎች ወያኔ በእንደዚህ ያለ መንገድ ነው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻችንን ለድርቅ እና ለረሀብ የሚዳርገው ብለዋል።

ከአስራ አንድ ሚሊዮን በላይ ህዝብ በተራበበት በዚህ የጭንቅ ጊዜ የሳውዲ መንግስት በሀገራችን ዘርቶ እና አጭዶ በርካታ ሰብል ሰብስቦ ከጎተራው አስገባ የሚል ዜና ሲሰማ ግራ የሚያጋባ እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን ሳያጣ ያጣው እና በወያኔ እኩይ ፓሊስ ተተብትቦ እግር ከወርች የተያዘውን ገበሬ ምሬት ዘገባው ሊያባብሰው እንደሚችል ተጠቁሟል።

ከአገሪቱ ዜጎች 15 በመቶ ወይም አስራ አንድ ሚሊዮን ያህሉ ለከፍተኛ የረሃብ አደጋ ተጋልጠ በተባበሩት መንግስታት አስተባባሪነት ከአለም አቀፍ እርዳታ ሰጭ መንግስታት በሚገኘው የእህል ምጽዋት ህይወቱን ለማቆየት በሚገደድበት አገር ለእርሻ ምርት የሚሆን ለም መሬት ለባዕድ አሳልፎ በመሸጥ ለሃብታሞችና ለጥቂት የወያኔ ስግብግብ ባለሥልጣናት መጠቀሚያ ማድረግ በትውልድና በአገር ላይ የሚሰራ ከፍተኛ በደል እንደሆነ ህዝባችን ሊገነዘብና ይህ ደባ በኢኮኖሚ ጥቅሙ ላይ ብቻ ያነጣጠረ ሳይሆን በመኖር ዋስትናውና በግል ህይወቱ ላይ የሚደረግ የጠላት ደባ በመሆኑ ህዝባችን ይህንን ሥርዓት ከጫንቃው ላይ ለማሽቀንጠር የተጀመረውን ሁለገብ ትግል ከምር ሊደግፍና በፊልሚያውም ሊሳተፍ እንደሚገባ የግንቦት 7 ንቅናቄ እምነት መሆኑ በተደጋጋሚ ሲገለጽ መቆየቱ ይታወቃል።

## እነመለስ እየተሸበሩ ...

( ከገጽ 1 የዞረ)

ይህ የመለስ አገዛዝ ያወጣው መግለጫ የአሜርካ መንግሥት በዓመታዊዉ የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ሪፖርቱ ለጠቀሳቸው አሳሳቢ ወንጀሎች እንደ መከላከያ አድርጎ የተጠቀመው ሰብዓዊ መብቶች በአገሪቱ ያለመጣሳቸውን ሊገልጽ የሚችል ተጨባጭ ማስረጃዎችን በማቅረብ ሳይሆን "የሰራሁዋቸው ቀና ነገሮች ከግምት ውስጥ አልገቡልኝም" ከሚል ጭፍን አስተሳሰብ በሪፖርቱ ውስጥ የሰፈሩትን ጭብጦች "መሰረተ ቢስ ወሬዎች" እና "አሉባልታ" በሚል ተራ አረፊተ ነገሮች ደጋግሞ ለማጣጣል በመሞከር እንደሆነ ታውቆአል ። በሪፖርቱ መጨረሻ ላይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለያንዳንዱ ውንጀላ መልስ ይዞ እንደሚቀርብ የገለጸ ቢሆንም ወያኔ የተካነበት የሚመስለው ነገር ግን ከጊዜ ብዛትና በተደጋጋሚ በፈጸማቸው ድርብርብ የአደባባይ ላይ ወንጀሎች እየደበዘዘ በመጣው የተለመደ ትግሬቱ "አይናችሁን ያዙና ላሙኝችሁ ከሚለው የሞኝ ወሬ" ያለፈ ምንም ማስረጃ ሊያገኝ እንደማይችል ግልጽ ነው ተብሎአል።

(ወደ 4 ገጽ ዞሯል)

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን።
g7radio@ginbot7.org

# ሃይለ ሀሳብ

## ሐይማኖት የፖለቲካ መሳሪያ አይሆንም!

ከዝግጅት ክፍላችን

አገራችን ኢትዮጵያ ጥንትም ሆነ ዛሬ የተለያዩ ሐይማኖቶች አገር መሆኗን ህዝቦቿም ሆኑ ታሪክ ላፍታም ቢሆን የማይዘልሉት ሀቅ ነው። ይህ ሀቅ ደግሞ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ብዙ አገሮች የሚጋሩት ሀቅ ነው። ሆኖም የሐይማኖት ነገር ሲነሳ አገራችን ኢትዮጵያን ከሌሎች አገሮች ልዩ የሚያደርጓት ብዙ ነገሮች አሉ። እነዚህን ብዙ ነገሮች የዛሬው የህሊና እስረኛ ቴዲ አፍሮ "ሸመንደፈር" በሚለው ዜማው አጣፍጦ ለህዝብ አቅርቧል፤ ዛሬ ይህ ጽሁፍ እንደ ምሳሌ ወስዶ የሚመለከተው እነዚያኑ ቴዲ አፍሮን ለእስር የዳረጉትን ትልልቅ የእውነት ስራዎች ነው። ኢትዮጵያን ከሌሎች አገሮች ልዩ የሚያደርጋት የብዙ ሐይማኖቶች አገር መሆኗ አይደለም፤ ኢትዮጵያን ልዩ የሚያደርጋት የተለያየ ሐይማኖት የሚከተሉ ህዝቦች ለረጂም ዘመን ተከባብረው በጉርብትና የኖሩባትና የሚኖሩባት አገር መሆኗ ነው፤ በተለይ ሦስቱ በአንድ አምላክ የሚያምኑ ማለትም የእስልምና፣ የክርስትናና የአይሁድ ሐይማኖት ተከታዮች በርቀት ብቻ ሳይሆን እጅግ ተቀራርበው በኖሩባቸውም በብዙ አካባቢዎች በመካከላቸው ምንም አይነት የጎላ ችግር ሳይፈጠር ለብዙ ዘመን ተከባብረው ኖረዋል። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥልጣን በክርስትና እምነት ተከታዮች ስር በነበረበትና የኢትዮጵያ መንግስት ከሐይማኖት ጋር ቀጥተኛ ግኑኝነት በነበረው በእነዚያ በሺ በሚቆጠሩ ዐመታትም ውስጥ ቢሆን ኢትዮጵያን በክርስትና ወይም በእስልምና ሐይማኖት ጥላ ስር አስተባብሮ አንድ ለማድረግ ከተደረጉ ግጭቶች ውጭ የኢትዮጵያ ህዝብ በሐይማኖት ተከፋፍሎ የተዋጋበት የታሪክ ወቅት የለም።

ከኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙሮች አንዱ በሆነው በፊሊጶስ የውሃ ጥምቀት የተጠመቀው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አገሩ ሲመለስ የክርስትናን መሠረተ ሃሳቦች ይዞ እንደመጣ ብዙ ሰዎች ያምናሉ፤ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በአራተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ የኖረው ንጉስ ኤዛና ክርስትናን የመንግስቱ ሐይማኖት እንዳደረገው ታሪክ ይናገራል።ይህ ከሆነ ከ300 ዐመታት በኋላ የነቢዩ መሐመድ ተከታዮች የነቢዩ የትውልድ ስፍራ ከሆነውና ዛሬ የእስልምና ትልቁ ቅዱስ ቦታ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ሲሰደዱ የፍቅር እጆችዋን ዘርግታ የነቢዩ መሐመድን ተከታዮች ተቀብላ ያስተናገደችው ኢትዮጵያ ነበረች።ለምሳሌ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የመጀመሪያው ፍልሰት (ሀጅራ) በመባል የሚታወቀው ይሄው የነቢዩ መሐመድ ተከታዮች ወደ ኢትዮጵያ የደረጉት የስደት ጉዞ ነው። እንግዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ እነዚህ ሁለት ታላላቅ የዓለም ሐይማኖቶች ማለትም ክርስትናና እስልምና የጉርብትና ኑሮ ከጀመሩ ከ1300 አመታት በላይ ተቆጥረዋል። ክርስትናና እስልምና ተከባብረው የኖሩበትን የረጂሙ ን ዘመን ታሪክ ትተን መለስ ዜናዊ በይፋ ባአደባባይ የተቀበለውን ያለፈውን አንድ መቶ አመት ታሪካችንን ብቻ እንኳን ብንመለከት ሐይማኖተ አጥባቂ የነበሩት የምኒልክና የኃይለስላሤ መንግስታትና ስለ ሐይማኖት ብዙም ግድ ያልነበረው የደርግ መንግስት በጥቅል ኢትዮጵያን ባስተዳደሩባቸው 110 አመታት ውስጥ ኢትዮጵያውያን የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች ይህ ነው ተብሎ ሊጠቀስ በሚችል መልኩ ደም ተፋሰው አያውቁም።

እንግዲህ የሐይማኖት መከባበርን በተመለከተ ያለፈው ታሪካችን ይህንን ይመስላል! የዛሬውስ? መቼም ነገሩ በጥባጭ እያለ ንፁህ ውሃ አይጠጣም ነውና የራሱ የስልጣን ዘመን እስከረዘመለት ድረስ ስለ ኢትዮጵያም ሆነ ስለህዝቦቿ ደንታ የሌለው አመፀኛው መለስ ዜናዊ ቄስ አድርጎ ያሰለጠናቸውን ካድሬዎቹን ጥምጥም አስጠምጥሞ መስጊድ በመላክ እንደ ሼክ አድረጎ ያሰለጠናቸውን ደግሞ ኮፊያ አስለብሶ ቤተክሪስቲያን እንዲሳለሙ በማድረግ ተከባብረው በሠላም የኖሩትን ኢትዮጵያውያን እስላሞችና ክርስቲያኖች እንዲጋጩና ደም እንዲፋሰሱ እያደረገ ነው።እንደ ቆላ ዝንብ ያገኘው ነገር ውስጥ ሁሉ አይኑን ጨፍኖ ጥልቅ ማለት የሚወደው መለስ ዜናዊ ግራና ቀኝ እየጨረ ያመጣው መዐት አልበቃ ብሎት ዛሬ የኢትዮጵያውያንን ህብረትና አንድነት እጅግ አደገኛ በሆነና ከተለኮሰ በማይጠፋ እሳት ለማጥፋት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው።

እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከ1998- 2001 ባለው ጊዜ በደምቢዶሎ፣ በበጊ፣በጊዳሚ፣በጅማና በአካባቢው፣ እንዲሁም በድሬደዋና በጂጂጋ ከተማዎች በእስልምናና በክርስትና እምነት ተከታዮች መካከል በተፈጠረ ግጭት በህይወትና በንብረት ላይ ከፍተኛ አደጋ ደርሷል። በተለይ ለአራት ተከታታይ ቃናት የዘለቀውና የ10 ሰዎችን ህይወት የቀጠፈው የጅማው ግጭት- ለመሆኑ ኢትዮጵያ የፀጥታ አስከባሪዎች አሏት ወይ የሚል ጥያቄ እያስነሳ ብዙ ታዛቢዎችን አስገርሟል። የዲሞክራሲ ጥያቄ ያነገቡ ሠላማዊ ሠልፈኞች ላይ ተኩስ ከፍቶ ከ200 ሰዎች በላይ የገደለው መለስ ዜናዊ ህዝብ እስላምና ክርስቲያን ተባብሎ ለአራት ቀናት ሲጨፋጨፍ ዝም ብሎ ማየቱ ቀድሞውኑም ቢሆን ሆን ብሎ ችግሩን የፈጠረው እሱ እራሱ መሆኑን በግልፅ ያሳያል። ይህንኑ የጅማውን ግጭት አስመልክታ የቢቢሲዋ ዜና ዘጋቢ ኤንበር ሄንሻው በወቅቱ እንዲህ ነበር ያለችው፡ "አንዳንድ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ መሆን የጀመሩት የሐይማኖት በዓላቸውን ለማክበር የወጡ ክርስቲያኖችን የአካባቢው ሙስሊሞች ለማስቆም ሲሞክሩ ነው። እነዚህ ሁለት እምነቶች በመግባባት ለብዙ ዘመን ጎን ለጎን አብረው የኖሩ በመሆናቸው ይህ ግጭት ለብዙ ኢትዮጵያውያን ከዬት እንደ መጣ የማይታወቅ ዱብ ዕዳ ሆኗል"

አዎ! የመለስ ዜናዊን ትክክለኛ በህሪይ በውል ላልተረዳ ሰው ይህ ዘግናኝ ግጭት ከዬት እንደ መጣ ላይታወቀው ይችላልና በእርግጥ ነገሩ ዱብ ዕዳ ነው።ይህ በእንዲህ እንዳለ የችግሩን መንስኤ እንዲመረምር ሐላፊነት የተሰጠው የፌዴራል ፖሊስ መሆኑ ደግሞ በእርግጥም ብዙ ሰዎች የጥፋቱን ትክክለኛ ባለቤት የማወቅ ዕድል አይኖራቸውም።የፌዴራል ፖሊስ ቃል አቀባይ የሆነው ደምሳሽ ኃይሉ የጅማውን ችግር አስመልክቶ ለቢቢሲዋ ጋዜጠኛ እንዲህ ሲሉ ተናግሮ ነበር- "ይህ ቀውስ የተቀሰቀሰው ህዝብን ከህዝብ ጋር በማጋጨት ርካሽ የፖለቲካ አላማቸውን ከግብ ለማድረስ በሚፈልጉ ጥቂት ሰዎች ነው" በእርግጥም አቶ ደምሳሽ ስሙ እንደሚያመለክተው ዋናውን እውነት ደምስሶ አለፈው እንጂ የችግሩ ባለቤቶች የርካሽ ፖለቲካ ነጋዴዎች መሆናቸውን መደበቅ አልቻለም። ስምን መልአክ ያወጣዋል ይሏል እንደ አቶ ደምሳሽ ነው! የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ሌላ ሌላውን ሥራ ሁሉ ትቶ ጅማ ውስጥ የተከሰተውን ችግር ብቻ ሲመረምር ቢከርም እንደ ቴዲ አፍሮ ከመንገድ ላይ ሰዎች ሰብስቦ ያስቀጣ እንደሆነ ነው እንጂ የኢትዮጵያ ህግማ ትክክለኛውን ጥፋተኛ ፈልጎ እንዲያገኝ አይፈቅድለትም- ምክንያቱም በዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጠረው የሐይማኖት ችግር ጥፋተኛው፣ ህጉና መርማሪው፣ ሁሉም አንድ አካል አንድ ሰው ነው፤ይህ ሰው ደግሞ እራሱን መርምሮ እራሱን ጥፋተኛ አያደርግም።

ለመሆኑ የመለስ ዜናዊ መንግስት እነዚህ ከ1300 ዐመታት በላይ ተከባብረው የኖሩ ሐይማኖቶች እንዲጋጩ የሚያደርገው ለምንድነው? የመለስ ዜናዊ መንግስት ከምን ጊዜውም በበለጠ መልኩ ለአደጋ የተጋለጠበት ወቅት ቢኖር ያ' ወቅት ዛሬ ነው። የስሜኑ መሬት ሽያጭ የቀሰቀሰው የህዝብ ቁጣ፣ የሶማልያው ዘመቻ ያስከተለው የፖለቲካ ክስረት፣ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ቀውስ ያስከተለው ጫናና አዲሱ የኦባማ አስተዳደር ለአምባገነኖች የሰጠው ማስጠንቀቂያ የመለስ ዜናዊን መንግስት አንቀጥቅጦታል።ይህ እሱ የሚተኛበት መኝታ ቤት እስካልተነካና ሰደዱ ሌሎችን አስካቃጠለለት ድረስ የራሱ መኖሪያ ቤት ላይም ቢሆን እሳት ከመጨር ወደ ኋላ የማይል ጨካኝ ሰው እስከዛሬ ያደረሰው በደል አልበቃ ብሎት ኢትዮጵያን አንዴ ከተቀጣጠለ ወደማይበርድ እሳት ውስጥ እየከተታት ነው። መለስ ዜናዊ አስራ ስምንት ዐመት ሙሉ ቢፍቀው ቢፍቀው አልጠፋልህ ያለውን የኢትዮጵያዊነት መንፈስ ዛሬ እስላምና ክርስቲያን በሚል እሳት ሊያቃጥለው እየሞከረ ነው። የኢትዮጵያ የክርስትና እምነት መሠረት ከሆነችው ከትግራይ መሬት የበቀለው ይህ እሳት ጫሪ ግለሰብ የኢትዮጵያ ህዝብ ለአገሩና ለሐይማኖቱ ቀናኢ መሆኑን በሚገባ ያውቃል። ስለዚህም ነው ትናንት በመሬቱ ዛሬ ደግሞ በሐይማኖቱ

እየመጣ የዚህን ጨዋ ህዝብ ትዕግስት ሌት ከቀን የሚፈታተነው።

መለስ ዜናዊን ከአሁን በኋላ ድምፁን ሰጥቶ የሚመርጠው ሰው ቀርቶ በመገናኛ ብዙኋን እንኳን ስሙ ሲጠራ መስማት የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ የለም። መለስ ዜናዊ ባለፉት 18 ዐመታት በሰራቸውና ወይም መስራት ሲገባው ባልሰራቸው ስራዎች የተነሳ የኢትዮጵያ ህዝብ ክፉኛ ተቆጥቷል፤ስለሆነም ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ከመለስ ርቋል መለስም ከኢትዮጵያ ህዝብ ርቋል። ስለዚህ ይህ ጨካኝና ተስፋ የቆረጠ ሰው ያ' በግድ የያዘው ስልጣን ከእጁ እንዳይወጣ ለማድረግ ያለው አማራጭ አንድ ብቻ ነው እሱም ከዚህ ቀደም የጎሳ አጥር ገንብቶ ያራራቀውን የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ ደግሞ በሐይማኖት አጣልቶ ጭራሽ እንዳይገናኝና በአገሩ ጉዳይ እንዳይመክር ማድረግ ነው። ይህ በፖለቲካ ይዘቱ ርካሽ በማህበራዊ ገጽታው ደግሞ እጅግ በጣም አደገኛ የሆነ የክፋት ጅምር አንዴ ሙሉ መልኩን ከያዘ መመለሻ የለውምና የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ሁሉ ከወዲሁ ልያስብበት ይገባል። ከጠመንጃ ጋር አድጎ በጠመንጃ ሥልጣን የያዘው መለስ ዜናዊ ችግር ውስጥ በገባ ቁጥር ዞር ብሎ የሚመለከተው ያንኑ ያደገበትን ጠመንጃውን ብቻ ነው።ዛሬ ግን ያ' ለሥልጣን ያበቃው ጠመንጃ ከሥልጣን ሊያስወግደውም እንደሚችል የተረዳው መለስ ዜናዊ እጁ ላይ የቀረውን የመጨረሻውን ካርድ መጫወት ጀምሯል።መለስ ዜናዊ 18 ዐመት ሙሉ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ተዋግቶ የተማረው ነገር ቢኖር ህዝብን ማሸነፍ እንደማይችል ነው፤ ስለሆነም ዛሬ ስልቱን ቀይሮ ህዝብን ከህዝብ ጋር ማዋጋት ጀምሯል።በዚህ መለስ ዜናዊ በጀመረው ህዝብን ከህዝብ ጋር የማዋጋት ስትራቴጂ አሸናፊም ተሸናፊም አይኖርም፤ ይህ የግል የሥልጣን ሱስን ለማርካት ብቻ የሚደረግ ጭፍን ሩጫ አገራችንን ከድጡ ወደ ማጡ ያዘቅጣት እንደሆነ ነው እንጂ መለስማ የፈለገውን ነገር ቢያደርግ የስልጣን ዘመኑን ማስረዘም አይችልም።አንድ ግልፅ የሆነ ነገር ቢኖር መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያን በቀላሉ ወደማትወጣው የእርስ በርስ የሐይማኖት ጦርነት እሳት ውስጥ እየማገዳት ነው።

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች አንድ እርምጃ ወደ ፊት በተጓዙ ቁጥር እንደ ዐመለኛ በቅሎ የሚደነብሩት መለስ ዜናዊና የበረሐ ጓደኞቹ ኢትዮጵያ ውስጥ እነሱ ክርስትና ያላነሱት ተቃዋሚ እንዳይኖር ከወሰኑ ቆይቷል። በአንድ በኩል የተቃውሞ ፖለቲካ እንዲኖር በህግ መፍቀድ በሌላ በኩል ደግሞ ህጉን ተግባራዊ ያደረገውን ሁሉ እያሰሩ ቃሊቲ መላክ - አንድን ሰው እጅና እግሩን አስሮ ዋኝተህ ውጣ ብሎ ባህር ላይ ከመጣል ተለይቶ አይታይም።ከኛ ሌላ መሪ ከኛም በላይ አዋቂ የለም የሚሉት እነዚህ ሳይመሽ የነጋባቸው ትምክህተኞች ጥሏቸው የገሰገሰውን የኢትዮጵያ ህዝብ እንኳን ከፊቱ ሆነው ሊመሩት ከኋላው ሆነው መከተልም ተስኗቸዋል።

መለስ ዜናዊ ይህን እሱ እራሱ ሆን ብሎ የቀሰቀሰውን የሐይማኖት ችግር አስመልክቶ በቅርቡ ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጥ እንዲህ ነበር ያለው *"የሐይማኖት እኩልነት ሳይሆን የማግለል አስተሳሰብ የሚያራምድ በሽታ የተጠናወታቸው ግለሰቦች አሉ፤ ይህን ኋላ ቀር የማግለል አመለካከት የሚያስተናግዱ አንዳንድ የሐይማኖት መሪዎች ቄሶች ወዘተ አሉ፤ይህን መፈክር በማራገብ ብጥብጥ ለመፍጠር የሚጥሩ የውጭና የውስጥ የፖለቲካ ኃይሎችም አሉ"* እውነትን መካድና አገርን መናድ የማይሰለቸው መለስ ዜናዊ አንዳንድ ግለሰቦችን፣ ቄሶችንና ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ሳይታመሙ በሽተኛ አደረጋቸው እንጂ ሐኪምም ጠበልም በማያድነው ደዌ የተለከፈ በሽተኛ ሰው ቢኖር መለስ ዜናዊ ብቻ ነው።ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ የሐይማኖት እኩልነት ባልነበረበት ዘመን እንኳን ከ1300 ዐመታት በላይ ተከባብረው የኖሩት ክርስትናና እስልምና ዛሬ የሐይማኖት እኩልነት ተረጋግጧል በሚባልበት ወቅት እንዲህ ደም የሚያፋስሳቸው ምንድነው? ይህ በፊውዳሉና በወታደራዊው ስርአቶች ውስጥ ያልታየ የሐይማኖት ችግር ዛሬ የኢትዮጵያ የዲሞክራሲ አባት ነን ባዮች አገርቱን እየመሩ መከሰቱ ብዙ አፍቃሬ ወያኔ የፖለቲካ ታዛቢዎች አቋማቸውን እንዲመረምሩ አስገድዷቸዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ በየዘመኑ የደረሱበትን እጅግ ፈታኝ የሆኑ የመከራ ጊዜዎች በጽናት ተቋቁሞ ለዛሬ የበቃ አስተዋይ ህዝብ ነው።ይህ እሱ አስተዋይ ሆኖ ለአስተዋይ መሪዎች ያልታደለ ህዝብ መሪዎቹ ባስጨነቁትና ባሰቃዩት ቁጥር አገሩን የሚክድ ወይም የሚረሳ ህዝብ አይደለም፤የኢትዮጵያ ህዝብ እናት አገሩን ኢትዮጵያንና መሪዎቹን ነጣጥሎ የሚመለከት ህዝብ ነው፤ለምሳሌ ንብረቱን የቀማውና ልጆቹን የገደለበት መንግስቱ ኃ/ማሪያም የእናት አገር ጥሪ ሲያደርግ የኢትዮጵያ ህዝብ ጥሪውን አክብሮ ጦር ሜዳ ሄዶ ተሰውቷል፤ ይህ ብቻ አይደለም የአክሱም ሐውልት ለወላይታ ምኑ ነው ያለውና የወላይታን ህዝብ ከፍላጎቱ ውጭ አዲስ ቋንቋ ካልተናገርክ ብሎ ያላግጥ የነበረው መለስ ዜናዊም ተመሳሳይ ጥሪ ሲያደርግ ቀድሞ ጥሪውን ከተቀበሉት ህዝቦች አንዱ የወላይታ ህዝብ ነበር። የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬም ለአንድነቱና ለነፃነቱ በተጠንቀቅ ቆሟል፤ በተለይ ዛሬ ለሰብዓዊ መብቱና ለአንድነቱ እስከ ሞት ድረስ የቆረጡ ልጆቹ ከጎኑ በቆሙበት ወቅት ይህ ጀግና ህዝብ የከፋፋዮችን ሴራ በጣጥሶ ላንዴም ለመጨረሻም የአገሩ ሥልጣን ብቸኛ ባለቤት የሚሆንበት ጊዜ እጅግ በጣም ቅርብ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሐይማኖት አንድ ለአንድ ከፈጣሪው ጋር የሚያገናኘው መንፈሳዊ መንገድ እንጂ የአንድነቱ ምንጭ እንዳልሆነ በሚገባ የሚገነዘብ ህዝብ ነው። ዛሬ እስላም የሆነ ሰው ነገ ክርስቲያን ክርስቲያን የነበረው ደግሞ እስላም ሊሆን ይችላል፤ኢትዮጵያዊነት ግን ተወልደን የምንኖርበት ክብራችን ስንሞት ደግሞ የምንቀበርበት ማተባችን ነው። ስለዚህ በታሪኩ ሁሉ ጠላቶቹን እንዳሳፈረ የኖረው የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬም በክርስትናና በእስልምና ስም የሚከፋፍሉትን ጠላቶቹን አሳፍሮ በእኩልነት ላይ የተመሠረተች ኢትዮጵያን ይገነባል፤ይህንን የሚጠራጠሩ የሚኖሩ አይመስለንም፤ ቢኖሩም የሚጠራጠሩት የወያኔን መወገድ ወይም የኢትዮጵያን ህዝብ ጀግንነት ሳይሆን እነሱ እውነትም ከዚህ ጀግና ህዝብ መፈጠራቸውን መሆን አለበት።

---

እነመለስ እየተሸበሩ ... ( ከገጽ 2 የዞረ)

የግንቦት 7 ድምጽ የአዲስ አበባ ሪፖርተር ያነጋገራቸው አንድ እዚያው ውጭ ጉዳይ ሚንስቴር ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያ "የመግለጫው አንድ የመከራከሪያ ነጥብ ሪፖርቱ ኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶችን በማክበር ረገድ ላስመዘገበቻቸው ድሎች ምንም ቦታ አልሰጠም" የሚል ሲሆን፣ "ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ፣ የመደራጀት፣ ተቃውሞን በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ የመግለጽ፣...ወዘተ ህገመንግስታዊ መብቱች በሙለ መጨፍለቃቸው በማያከራከርበትና ለማስተባበልም አስቸጋሪ በሆነበት ሁኔታ መንግሥታችን አታካራ ለመግባት ለምን እንደፈለገ ግልጽ ነው በማለት መንግሥት ይህን ማድረግ ችሮታ እንጂ ግዴታ ሊመስላቸው እስከማይችል ድረስ እራሳቸውንና ደናቁርት ካድሬዎቻቸውን በማሳመን ያዙኝ ልቀቁኝ ማለቱ የውድቀት መቃረቢያ ወቅት አምባገነኖች ሁሉ የሚጠቀሙበት የእብሪት ባህሪይ መግለጫ ቋንቋ ነው ብለዋል::

አያይዘውም "አለቆቼን ግራ ያጋባቸውና ያስደነገጣቸው ትናንት በጆርጅ ቡሽ የሥልጣን ዘመን ህጻን ከሽማግሌ ሳይለይ በአጋዚ ጥይት በጠራራ ጸሃይ ስጨፈጨፍ ያላወገዘኝ የቅርብ ወዳጄ የሚለው አገር የጥይት ድምጽ በአደባባይ በማይሰማበት በዛሬው ቀን እየወሰድኩት ያለው እርምጃ ህይወቴን ሥልጣን ላይ ለማቆየት ምንያህል ወሳኝ እንደሆነ እንዴት ተዘንግቶት ነው ጠላቶቼን የልብ ልብ በሚሰጥ ቋንቋ የሚያወግዘኝ?" በሚል ምሬት እንደሆነ ገልጸዋል ::

በተያያዘ ዜና "የባራክ ኦባማ መንግስት አሜሪካ በኢትይጵያ ላይ ያላትን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ይለውጣል ብለው የሚያምኑ ተቃዋሚዎች ቅዠታሞች ናቸው፣ እኔና አሜሪካም ጥሩ ግንኙነት አለን" በማለት ወያኔ ሌት ተቀን የሃሰት ፕሮፖጋንዳ በተከታታይ መንዛት መቀጠሉ ተዘግቦአል:: ይሁን እንጂ ይህንን የሃሰት ፕሮፖጋንዳውን በሚቃረን መልኩ አሜሪካ ኢትዮጵያን ለመጉዳት ዓላማ እንዳላት ግልጽ እየሆነ መጥቶአል ሲል ላለፉት 18 ዓመታት በስዩም መስፍን የሚመራው የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር ያወጣው መግለጫ አሜርካንን አማሮአል:: ከሁሉም ኢትዮጵያውያንን ያስገረመው ግን በውጭ ጉዳይ ሚንስቴሩ መግለጭ ውስጥ ወያኔ የሰብዓዊ መብት አያያዝ ሪኮሩዱን ከአሜሪካ ጋር ለማወዳደር "አሜሪካ እንጂ ኢትዮጵያ የሰውን ልጅ ለማሰቃየት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን አታመርትም አታስመርትምም ፣ የዓለም አምባገነን መንግስታትም የሰውን ልጆች ለማሰቃየት የሚጠቀሙበትን መሳሪያ በአብዛኛው የሚገዙት ከአሜሪካ ነው በማለት ምን ያህል በዚህ አባባል የራሱን እኩይ ተግባር እንዳጋላጠ ሳይታወቀው አሜሪካን ለመክሰስ መሞከሩ እንደሆነ ታውቆአል::


## የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ
## የሥርጭት ሞገድ ለውጥ አድርጓል።

በዚሁ መሰረት ከአሁን ቦኋላ **በ7485 KHZ በ41 ሜትር ባንድ** እና **በ9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።